
# ምዕራፍ ስድስት

## ዓለምአቀፋዊነት ወይስ ብሔራዊነት?



**የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤

- ❖ የዓለምአቀፋዊንትንና የብሔራዊነትን ምንነትና ልዩነቶች ደረጃውን የጠበቀ የኢ.ምቋ በመጠቀም ታስረዳላችሁ፤
- ❖ ከዓለምአቀፋዊንትንና ከብሔራዊነት ጋር የተያያዙ የኢ.ምቋ ምልክቶችን በዕለት-ተዕለት ተግባቦት ውስጥ ከነሥነምልክታዊ ውበታቸው ትጠቀማላችሁ፤
- ❖ በዓለምአቀፋዊንትንና በብሔራዊነት ጥቅሞችና ጉዳቶች ዙሪያ በክፌል ውስጥ በመከራከር የግል አቋም ትይዛላችሁ፤
- ❖ ከምንባቡ ውስጥ የኢ.ምቋ ገላጭ ግሶችን ትለያላችሁ፤
- ❖ የኢ.ምቋ ገላጭ ግሶችን በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢው መንገድ ትጠቀማላችሁ፤
- ❖ የክርክር መሮሖችን በመከተል፤ ከተቃራኒ አቋሞች አንዱን ደግፋችሁ ትከራከራላችሁ።


## ቁልፍ ምልክቶች




አለምአቀፋዊነት




ጽንሰ-ሃሳብ



ምሁራዊ




አህጽሮት




ካፒታል




ተግዳሮቶች/ተግዳሮት




የአየር ንብረት ለውጥ



የአየር ብክለት




ነቃፊዎች/መንቀፍ




ራዕይ



ኢንተርኔት




ቴክኖሎጂ




አሜሪካ




ሳታላይት



የሚጻረሩ/መጻረር



እርምጃ መውሰድ




## ክፍለ ትምህርት አንድ


### የማነቃቂያ ጥያቄዎች

#### እይታዊ ንባብ

1. የሚከተሉትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ።
2. ሥዕሎቹን መሠረት በማድረግ ዓለምአቀፋዊነትና ብሔራዊነት የሚሉት ጽንሰሐሳቦችን ምን እንደሆኑ ለማስረዳት ሞክሩ።



ዓለምአቀፋዊነት



ብሔራዊነት

## የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. ለዓለማችን የሚበጃት ሀገሮች ዓለምአቀፍ ራዕይ ይዞ መሥራት ወይስ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ማተኮር? ምክንያታችሁን አስረዱ።
2. እያንዳንዱ ሀገር የራሱ ጉዳይ ላይ ብቻ ቢያተኩር በአሁኑ ወቅት የዓለም ስጋት የሆኑ ችግሮች፤ ለምሳሌ የአየር ንብረት ለውጥ፣ መፍትሔ የሚያገኝ ይመስላችኋል? ለምን?

## ምንባብ

መምህራችሁ ዓለምአቀፋዊነት ወይስ ብሔራዊነት? የሚለውን ምንባብ ሲያነቡ ሃሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን የምልክት አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ።

### ዓለምአቀፋዊነት ወይስ ብሔራዊነት?

ዓለምአቀፋዊነት እና ብሔራዊነት የዘመናችንን ሁለት አመለካከቶች የሚገልጹ ጽንሰሐሳቦች ናቸው። ቀለል ባለ አገላለጽ፣ አለምአቀፋዊነት በአለም ሀገሮችና ህዝቦች መካከል ያሉትን ልዩነቶች በማጥበብ አንድ የጋራ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሚደረገውን እንቅስቃሴ የሚወክል ቃል ነው። ብሔራዊነት ደግሞ የዚህ ተቃራኒ የሚመስል ጠባብ መልከአ-ፖለቲካዊ መዋቅርን የሚያመለክት ነው።

ምሁራዊ ጽሁፎች ዓለምአቀፋዊነትን፤ ኢኮኖሚያዊ ዓለምአቀፋዊነት፣ ባህላዊ ዓለምአቀፋዊነትና ፖለቲካዊ ዓለምአቀፋዊነት በማለት በሦስት ይከፍሉታል።

የዓለምአቀፋዊነት እንቅስቃሴ ከጀመረ የቆየ ቢሆንም ሰፋ ያለ እውቅና ማግኘት የጀመረው እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ መጨረሻ ላይ ነው። ከዚህ በኋላ እንቅስቃሴውም የበለጠ ጎልቶ መታየት ጀመረ። የዓለምአቀፋዊነት ሂደት በዋናነት ተጽእኖ ያደርጋል ተብሎ የሚታመነው በአምስት ዋናዋና ዓለምአቀፋዊ እንቅስቃሴዎች ሲሆን፣ እነሱም፤ ንግድ፣ ስራ፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሀብቶችና ተፍጥሮአዊ አካባቢ ናቸው።

የዓለም የገንዘብ ድርጅት የዓለምአቀፋዊነት አካል የሆኑ አራት ጉዳዮችን ለይቶ አስቀምጧል። እነሱም የሚከተሉት ናቸው፤ንግድና የገንዘብ ዝውውር፣ ካፒታልና ኢንቨስትመንት፣ ፍልሰትና የህዝቦች ዝውውርና የእውቀት ስርጭት ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪም አካባቢያዊ ተግዳሮቶች የሆኑ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ድንበር ዘለል የውሃና የአየር ብክለት እንዲሁም በውቅያኖሶች ላይ የሚደረግ ከመጠን ያለፈ የአሳ ማስገር ከዓለማአቀፋዊነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንዲሆኑ ተደርገዋል።

ዓለምአቀፋዊነትን የሚያራምዱ ወገኖች ሦስት ዋና ግቦች አላቸው። አንደኛው፤ በአካባቢያዊና በብሄራዊ ደረጃ የተወሰኑ ጠባብ አመለካከቶችን በማስወገድ ዓለምን ወደ አንድ ወጥና ሁሉን አቀፍ የሆነ አመለካከት ማምጣት ነው። ሁለተኛው፤ ሀገሮች እርስ በእርስ የሚደጋገፉበት፣ አንዱ ለሌላኛው አስፈላጊ የሚሆንበትና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ዓለምአቀፋዊ ትስስር መፍጠር ነው። የመጨረሻውና ሦስተኛው ግብ ዓለምአቀፋዊ ማኅበረሰብ መመሥረት ነው። ይህ ራዕይ የሚረጋገጠው ደግሞ ሀገሮች ብሔራዊ ድንበሮቻቸውን ለነጻ የገንዘብ፣ የእቃዎች፣ የአገልግሎቶች ፣ የሰዎች፣ የቴክኖሎጂና የመረጃ ዝውውር ክፍት ሲያደርጉነው። በዚህ ዓለምአቀፋዊ አስተሳሰብ ውስጥ “እኛ” እንጂ “እኔ” ቦታ የለውም። ዛሬ በሰዓት ብዙ ሺ ኪሎሜትሮች መጓዝ የሚችሉ ፈጣን ባቡሮችና ጄቶች፣ የምድርና የአየር የመጓጓዣ መንገዶችን ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት የዓለምአቀፋዊነት አካል ነው። እንደ ኢንተርኔት፣ ሳታላይት ቴሊቪዥኖች፣ ሞባይሎችና ወዘተ ያሉ ፈጣን የመገናኛ መንገዶችን በሁሉም የዓለም ክፍል ዳርቻዎች ለማድረስ የሚደረገው ጥረትም የዚሁ እንቅስቃሴ ውጤቶች ናቸው። በተጨማሪም፤ ሀገሮችን በፍጥነት ለማገናኘት ያለሙት ሀገርና አህጉር አቋራጭ የባቡርና የአስፓልት መንገዶች በሙሉ ይህንኑ ዓለምን ወደ አንድ ማኅበረሰብ የማምጣትና በሀገሮች መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ የሚደረገው ጥረት አካል ናቸው።

የዓለምአቀፋዊነት አቋም ደጋፊዎች እንቅስቃሴው ውጤት እያመጣና ዓለምን ወደ ተሻለ መኖሪያነት እየለወጣት እንደሆነ በማስረዳት የበለጠ ጥረት እንዲደረግ እየቀሰቀሱ ነው። በአንጻሩ፣ እንቅስቃሴውን በጥርጣሬ የሚመለከቱና የሚቃወሙት አካላት፣ በዓለም ደረጃ እየተከሰቱ ያሉ የተለያዩ አለመረጋጋቶች የዓለምአቀፋዊነት እንቅስቃሴ ውጤቶች አድርገው ያቀርባሉ። በዚህ ምክንያትም የተረጋጋ የፖለቲካ ስርአትና የበለጸገ ኢኮኖሚ ያላቸው ሀገሮች መረጋጋታቸውንና እድገታቸውን ማስቀጠል የሚችሉት በብሄራዊነት ላይ በማተኮርና ይህንኑ የሚደግፉ ፖሊሲዎች በማውጣትና በማራመድ ነው ብለው ያምናሉ። ዓለምአቀፋዊነትን ወይም ብሔራዊነትን እንደ ተሻለ አማራጭ በማቅረብ መከራከር በብዙ ሀገሮች የምረጡኝ ቅስቀሳዎች ውስጥ በጉልህ ታይቷል። በቅርብ በሰሜን አሜሪካና በፈረንሳይ የተደረጉ ምርጫዎችን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። በእነዚህ ሁለት ያደጉ ሀገራት ውስጥ የተደረጉ ምርጫዎች

በሁለቱ ሀሳቦች ዙሪያ ያጠነጠኑ ነበሩ። እ.ኤ.አ.በ2016 ምርጫ አሸንፈው የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ለመሆን የበቁት ዶናልድ ትራምፕ ዓለምአቀፋዊነትን ከሚቃወሙት መካከል የሚመደቡ ናቸው። የምርጫ መፈክራቸው "አሜሪካን እንደገና ታላቅ ማድረግ!" የሚል ብሔራዊ ይዘት ያለው ነበር። በዚሁ አቋማቸው ምክንያት ስልጣን እንደጨበጡ ከወሰዷቸው እርምጃዎች መካከል አንዱ ሀገራቸውን ከፓሪሱ ዓለምአቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ማውጣት ነበር። አለማቀፋዊነትን የሚጻረሩ ሌሎች እርምጃዎችንም ወስደዋል። በተመሳሳይ መንገድም እ.ኤ.አ. በ2017 በፈረንሳይ ምርጫ አሸንፈው ስልጣን የጨበጡት አማኑኤል ማክሮን የዓለምአቀፋዊነት ደጋፊ ሲሆኑ፣ ለድል ካበቋቸው ቁምነገሮች አንዱ ይሄው አቋማቸው እንደነበረ ይታመናል። ፕሬዘዳንት ማክሮን ስልጣን እንደጨበጡ አሜሪካ ብትወጣም የፓሪሱ አለምአቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ቃል ገብተዋል።

የዓለምአቀፍዊነትና የብሔራዊነት ጠቃሚነትና ጎጂነት አሁንም የዓለም ህዝቦችን በሁለት ከፍሎ እያከራከረ ያለ ጉዳይ ነው።

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ ውስጥ የተማራችኋቸውን ምልክቶች ስለመለማመድና የምንባቡን ሃሳብ የተረዳችሁበትን መጠን ለመገምገም ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በቃል መልሱ።

1. በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል ከፍ ሲል ከተነበበላችሁ ምንባብ ተወስደው ወደ ኢ.ምቋ የተተረጎሙ ዐረፍተ ነገሮች ተቀምጠዋል። የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገሮቹን በሚገባ ካጠናችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንድ አንቀጽ ወስዳችሁ በኢ.ምቋ አንብቡ።
2. የምንባቡን መልእክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ጥያቄዎች የምንባቡን ሐሳብ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለመመዘን የቀረቡ ናቸው። ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ መሞከራችሁ በዓይን የመስማት ብቃታችሁንም ለማዳበር ይረዳችኋል። ስለዚህ መምህራችሁ ጥያቄዎቹን በኢ.ምቋ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ ተመልከቱና፣ ተገቢ መልሶችን በኢ.ምቋ አቅርቡ።

1. ዓለምአቀፋዊነት ምን ማለት ነው?
2. በምሁራዊ ጽሁፎች መሠረት የአለምአቀፋዊነት ዓይቶችን ዘርዝሩ
3. የዓለምአቀፋዊነት ሂደት በዋናነት ተጽእኖ ያደርጋል ተብሎ የሚታመነው ዓለምቀፋዊ

ጉዳዮች ምንድናቸው?

4. የዓለም የገንዘብ ድርጅት ያስቀመጣቸው የአለምአቀፋዊነት አካል የሆኑ እንቅስቃሴዎች ምንድናቸው?

5. በምንባቡ መሠረት ዓለምአቀፋዊነትን የሚያራምዱ ወገኖች ዋና ዋና ግቦች ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ።

6. ዓለምአቀፋዊነትን የሚያራምዱ ወገኖች የነደፏቸው ዋና ዋና ግቦች ሊሳኩ የሚችሉት በዋናነት ሀገሮች ምን አይነት እርምጃ ሲወስዱ ነው?

7. ከዓለምአቀፋዊነትና ከብሔራዊነት ደጋፊ የዓለም መሪዎች ሁለቱን ጥቀሱና ድጋፋቸውን ያሳዩበትን መንገዶች አስረዱ።

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ገላጭ ግሶች

### መልመጃ አንድ

ዓለምአቀፋዊነት ወይስ ብሔራዊነት? ከሚለው ምንባብ ውስጥ አምስት ገላጭ ግሶችን ለይታችሁ አውጡ። በመቀጠለም በአምስቱ ግሶች የኢ.ምቁ ዐረፍተ ነገር መሥርቱ።

**ምሳሌ:**

**ማጥበብ:** *ልዩ ልዩ ሀሳብ ጠበብ ጠበብ ቀጥሎ አንድ መሆን መቀጠል አስፈላጊ።*

(የሐሳብ ልዩነቶችን በማጥበብ በአንድነት መቀጠል አስፈላጊ ነው።)

### መልመጃ ሁለት

ዓለምአቀፋዊነት ወይስ ብሔራዊነት? ከሚለው ምንባብ ውስጥ ገላጭ ግሶች የያዙ አምስት ዓረፍተ ነገሮች ካወጣችሁ በኋላ ወደ የኢ.ምቁ ተርጉማችሁ አሳዩ።

**ምሳሌ:**

ዓለምአቀፋዊነት በዓለም ሀገሮችና ህዝቦች መካከል ያሉትን ልዩነቶች በማጥበብ አንድ የጋራ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሚደረገውን እንቅስቃሴ የሚወክል ጽንሰሐሳብ ነው።

**የተሰመረባቸው ምልክቶች ገላጭ ምልክቶች ናቸው።**

**ኢምቂ:** *ዓለም ማቀፍ ምን- ማለት ልዩ ልዩ አለም ውስጥ ያለ ሀገር መካከል ልዩ አለ እሱ መፍታት ጠበብ ጠበብ ከዛ አብሮ አንድ ኢኮኖሚ ፖለቲካ ማኅበረሰብ ማድረግ ዓላማ መሳካት መንቀሳቀስ እሱ ወኪል ሐሳብ።*

## መልመጃ ሦስት

### ክርክር

የምንባቡ ርዕስ ጥያቄያዊ እንደሆነ ልብ እንዳላችሁ ይታመናል። በምንባቡ ውስጥም ሁለት የሚቃረኑ የሚመስሉ አመለካከቶች ተገልጸዋል። የምትደግፉትን አመለካከት መምረጥ መብታችሁ ነው። ምርጫችሁ ግን በስሜት ላይ ሳይሆን በምክንያትና በመረዳት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይጠበቃል። መምህራችሁ ይህን ለመገምገም እንዲችሉ እንደየ ምርጫችሁ በሁለት ቡድን በመሆን በሚከተለው ርዕስ ላይ ተከራከሩ።

### የክርክር ርዕስ

*ኢትዮጵያ አሁን አለ ሁኔታ ጠቃሚ መከተል የቱ? መመልከት ዓለም ማቀፍ ወይም መመልከት ብሔራዊ ጥሩ መመልከት የቱ? ለምን መደገፍ ስጥ።*

(ለኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጠቃሚ የሆነው የዓለምአቀፋዊነት አመለካከት ነው ወይስ የብሔራዊነት? ለምን?)

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### የኢምቁ ናሙና ሰዋሰው

ከዚህ በታች የተቀመጡት አማርኛ ዐረፍ ተነገሮች በሙሉ ‹‹ዓለምአቀፋዊነት ወይስ ብሔራዊነት›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። ናሙናዎቹን በጥንቃቄ ከተለማመዳችሁ በኋላ ወደ ምንባቡ በመመለስ በኢምቁ አንብቡ።

1. **ኢምቂ:** *ዓለም ማቀፍ - ብሔራዊ ሁለት አሁን ዘመን መመልከት ማሳየት ሃሳብ ስም።*

   **አማርኛ:** ዓለምአቀፋዊነት እና ብሔራዊነት የዘመናችንን ሁለት አመለካከቶች የሚገልጹ ስሞች ናቸው።

2. **ኢምቂ:** *ዓለም ማቀፍ ምን- ማለት ልዩ ልዩ ዓለም ውስጥ ያለ ሀገር መካከል ልዩ*

*ኣለ እሱ መፍታት ልዩ ጠበብ ጠበብ ከዛ ኣብሮ ኣንድ ኢኮኖሚ ፖለቲካ ማኅበረሰብ ማድረግ ዓላማ መሳካት መንቀሳቀስ እሱ ወኪል ሐሳብ።*

**አማርኛ:** ዓለምአቀፋዊነት በዓለም ሀገሮችና ህዝቦች መካከል ያሉትን ልዩነቶች በማጥበብ አንድ የጋራ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሚደረገውን እንቅስቃሴ የሚወክል ጽንሰሐሳብ ነው።

3. **ኢምቂ:** *ዓለም ማቀፍ መመልከት ዓለም ሰዎች ሁሉ ሙሉ መደገፍ ኣይደለም።*

**አማርኛ:** የዓለምቀፋዊነት አመለካከት በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ሁሉ በአንድ ድምጽ የሚደግፉት አይደለም።

4. **ኢምቂ:** *ዓለም ማቀፍ መመልከት መደገፍ ሰው ኣለ እንደገና መቃወም ሰው ኣለ።*

**አማርኛ:** የዓለምቀፋዊነት አመለካከት ደጋፊዎችና ነቃፊዎች አሉት።

5. **ኢምቂ:** *ዓለም ማቀፍ መደገፍ ሰዎች መቀስቀስ መቀስቀስ መቀጠል ኣለ ምን-እንቅስቃሴ ኣለም መለወጥ ጥሩ ማድረግ ሂደት ስለዚህ መቀጠል ጥሩ መሻሻል ተጨማሪ ሙከራ ሙከራ ማድረግ ኣስፈላጊ መብርታት መበርታት።*

**አማርኛ:** የዓለምአቀፋዊነት አቋም ደጋፊዎች እንቅስቃሴው ውጤት እያመጣና ዓለምን ወደ ተሻለ መኖሪያነት እየለወጣት እንደሆነ በማሰረዳት የበለጠ ጥረት እንዲደረግ እየቀሰቀሱ ነው።